## መመሪያ ቁጥር 008/2013

## የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር

የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር፣ መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ መጓተት የሚያስከትለውን የፍትህ መጓደል ለማስቀረት የሚያስችል ወጥ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነት ሚዛናዊነት ተጠብቆ ዜጎች ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብታቸው ተረጋግጦ በዳኝነት ስርአቱ ላይ ያላቸው አመኔታና እርካታ እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ፣
ጉዳዮች እንደየመደባቸውና ተናጠል ባህሪያቸው ተለይተው በተመደበላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት አግኝተው ባለጉዳዮች በዳኝነት አገልግሎቱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማደረግ፣

የፍትህ መዘግየትን በማስቀረት በተገቢው ጊዜው ውስጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት የመስጠት ባህል እና አሰራር በመፍጠር ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል፣

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ አውጥቷል።

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**ሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓ/ም**
**አዲስ አበባ**

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ «የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ጉዳዮች ፍሰት አስተደደር መመሪያ›› ቁጥር 008/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ውስጥ ፡-

   1. **"የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር"** ማለት ፍርድ ቤት የቀረቡ ጉዳዮችን ሂደት በተቀላጠፈ መንገድ መምራት የሚያስችል አስተዳደራዊ ዘዴ ማለት ነው።

2. **"ቀነ ቀጠሮ"** ማለት በጉዳዮች ሂደት ውስጥ ለሚከናወኑ ድርጊቶች የሚሰጥ ጊዜ ማለት ነው፡፡
3. **"ጊዜ ገደብ"** ማለት ለጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ የተቀመጠ ጊዜ ማለት ነው፡፡
4. **"ውዝፍ ጉዳዮች"** ማለት በተቀመጠው አጠቃላይ ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያላገኙ ጉዳዮች ማለት ነው፡፡
5. **"እልባት ያገኙ ጉዳዮች"** ማለት በፍርድ፣ በትዕዛዝ ፣ በብይን፣ በውሳኔ ወይም በሌላ ህጋዊ ምክንያት የተዘጉ ወይም መቋጫ ያገኙ ጉዳዮች ማለት ነው፡፡
6. **"ተከራካሪ ወገኖች"** ማለት ለፍርድ ቤት በቀረበ የፍትሐብሔር ጉዳይ ተከፋይ የሆኑ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ጣልቃገብ፣ አመልካች፣ ተጠሪ፣ ይግባኝ ባይ፣መልስ ሰጪ፣ ዓቃቤ ህግ እና ሌሎች የክርክር ተካፋይ ሆኑ ተከራካሪዎች ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ተከራካሪ ወገኖችን ወክለው የሚቀረቡ ጠበቆችን እና ነገረ ፈጆችንም ይጨምራል፡፡
7. **"ሰብሳቢ ዳኛ"** ማለት ሦስትና ከዚያ በላይ የሆኑ ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት ሰብሳቢ ማለት ነው፡፡ አንድ ዳኛ የሚሰየምበትን ችሎት የሚመራ ዳኛንም የሚገልፅ ይሆናል፡፡
8. **"ፕሬዚዳንት"** ማለት በየደረጃው ያሉ የፍ/ቤት ፕሬዝዳንቶች ማለት ሲሆን ም/ፕሬዝዳንቶችንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር አላማ እና ግብ</u>

4. <u>ዓላማ</u>

የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ አላማ የስነ ስርአት ህጎችን በአተገባበር ረገድ የተሟላ በማድረግ ለተናጠል ጉዳዮች የተፋጠነ እና ጥራት ያለው ዳኝነት መስጠት የሚያስችል አሰራር መፍጠር ነው፡፡

5. <u>ግብ</u>

የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የጉዳዮች ሂደትና እልባት መስጫ ጊዜ መጓተትን ማስቀረት፣
2. ዜጎች በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ ያላቸው አመኔታና እርካታ መጨመር፣
3. ለጉዳዮች እንደየመደባቸውና ተናጠል ባህሪያቸው ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት መስጠት፣
4. ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች የጉዳዮች ሂደትና እልባት መስጫ ጊዜን ተገማች ማድረግ፣
5. በጉዳዮች ሂደት ውስጥ የሚከናወኑ ድርጊቶች ጥራት መጨመር፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ግልጽ ችሎት እና ቀዳሚነት

6. **ስለ ግልጽ ችሎት እና የፍርድ ቤት የስራ ሰዓት፡-**
   1. በህግ ተለይተው በዝግ ችሎት እንዲታዩ ከተመለከቱት በስተቀር የዳኝነት ተግባር በግልጽ የችሎት ማስቻያ አዳራሽ ውስጥ ይከናወናል፡፡
   2. የመንግስት የስራ መግቢያ እና መውጫ ሰአት እንደተጠበቀ ሆኖ የችሎት ስራ ጠዋት 3፡30 ሰዓት ከሰዓት በኂላ 8፡00 ሰዓት ላይ የሚጀመር ይሆናል፡፡
   3. ከላይ በንኡስ ቁጥር 2 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአካባቢው የአየር ንብረት ሁኔታ የፍ/ቤቱ ፕሬዝዳንት የተለየ የችሎት የስራ ሰአት እንዲኖር ሊወስን ይችላል፡፡
7. **ቀዳሚነት**
   1. ከሰበር ችሎት ወይም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተሰጠ ፍርድ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ መሠረት ወደ ስር ፍርድ ቤት ተመልሶ እንደገና እንዲታይ ወይም ሂደቱ እንዲቀጥል የተደረገ ጉዳይ ቅድሚያ ተሰጥቶት እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፣
   2. በንዑስ ቁጥር 1 ስር የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኞች በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም በሚቀርብላቸው አቤቱታ የጉዳዩን አስቸኳይነት ባህሪይ፣ የተከራካሪ ወገኖች የጤና እና የእድሜ ሁኔታ በመገንዘብ ከሌሎች ጉዳዮች በማስቀደም እልባት እንዲያገኝ ማድረግ ይችላሉ፣
   3. ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች እና የነፍሰጡር ሴቶች ተከራካሪ የሆኑባቸው ጉዳይ ተለይቶ ከሌሎች ቅድሚያ ከሚታዩ ጉዳዮች ጋር እልባት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

4. አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ከፍተኛ የልማት ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በተለይም የእግድ ትእዛዝ የተሰጠባቸው ከሆኑ ቅድሚያ ተሰጥቶት እልባት እንዲያገኙ ይደረጋል፤
5. ጉዳዮች በሂደት ላይ እያሉ የስነ ስርአት ህጉን መሰረት አድርጎ የሚቀርቡ የተለያዩ አቤቱታዎች የጉዳዮችን ሂደትና ፍርድ ጊዜን በማያጓትት መልኩ መፍትሔ የሚስጣቸው ይሆናል፤

## ክፍል አራት

## የቀጠሮ ፖሊሲ

### 8. የቀጠሮ ፖሊሲ መርህ

1. በመርህ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ቀጠሮ መስጠት የሚገባቸው አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ህግ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የስነ-ስርአት ድንጋጌዎች በተቀመጠው መሰረት ብቻ መሆን ይኖርበታል፤ የተሰጠው ቀጠሮም የሚከበርና እርግጥ መሆን አለበት፡፡
2. የጉዳዮች አቀጣጠር ቅደም ተከተል የጉዳዮች ውስብስብነት ሁኔታ፣ የተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ፣ እና የደረሱበት ሂደት ደረጃን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

### 9. ስለመጥሪያ

መጥሪያ የተላከለት ተከራካሪ ወገን መጥሪያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ወይም እሱ ቀርቦ ባለበት የታዘዘ እንደሆነ ከታዘዘበት ቀን ጀምሮ 15 (አስራ አምስት) ቀን ባልበለጠ ጊዜ ገደብ ውስጥ መከላከያ መልስ እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የጉዳዩን ውስብስብነት ወይም ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ዳኞች ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጡ የሚችሉ ሲሆን ይህ የሚሰጠው ጊዜ ግን በአንቀጽ 10 ከቀተመጠው ጊዜ መብለጥ የለበትም፡፡

### 10.የጽሁፍ ክርክር ቅብብሎሽ

ጉዳዩ ለሚመለከተው ባለጉዳይ መጥሪያ እንዲደርሰው ከታዘዘብት ቀን ጀምሮ 45 ቀን (በአርባ አምሰት ቀን) ባልበለጠ ጊዜ ገደብ ውስጥ መከላከያ መልስ፣ በይግባኝ ደረጃ ለሚታዩ ጉዳዮች እንደየአስፈላጊነቱ የመልስ መልስ ቅብብሎሽ የሚጠናቀቅበት ይሆናል፡፡ ከሌሎች

አካላት እንዲቀርብ የተጠየቀ ወይም ባለጉዳይ እጅ የሚገኝ የሰነድ ማስረጃ በዚሁ ጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

11. <u>በቀረቡ ጉዳዮች ላይ እልባት ስለመስጠት</u>

1. ክርክር እና ማስረጃ ተሰምቶ የተጠናቀቀ ከሆነ በዚህ መመሪያ የተቀመጠው የእልባት መስጫ የጊዜ ገደብ ጣራ መጠበቅ ሳያስፈልግ በ30 ቀናት ውስጥ እልባት መሰጠት አለበት፡፡
2. ከላይ ተራ ቁ. 1 ስር በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ እልባት ለመስጠት የማይቻልበት በቂ ምክንያት ሲኖር በዚህ መመሪያ ለጉዳዩ ከተቀመጠው አጠቃላይ እልባት የመስጫ የጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

12. <u>ስለቀጠሮ</u>

1. ቀነ ቀጠሮ የሚሰጠው መከናወን ለሚገባ ድርጊት ብቻ ይሆናል፡፡ ለቀጠሮ ምክንያት ለሆነው ድርጊት ክንውን በቂ የሆነ ቀነ ቀጠሮ መስጠት ይኖርበታል፡፡
2. የቀጠሮ አሰጣጥ ተግባር በዋናነት ጉዳዮች በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ ሂደታቸው ተጠናቆ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ በሚያስችል መልኩ መከናወን ይኖርበታል፣
3. የቀጠሮ አሰጣጥ ተግባር ከሰአት በፊት ወይም በኋላ መሆኑ ተለይቶ ቀንና ሰዓት ተጠቅሶ ለባለጉዳዮች በግልፅ በማሳወቅ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፣
4. የቀነ ቀጠሮ መጠን ወይም ርዝማኔ እንዲከናወን ወይም እንዲፈጸም የታዘዘው ድርጊት ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ የሚወሰን ይሆናል፣
5. ለድርጊቶች ክንውን የሚሰጠው ቀጠሮ እርግጥና የሚታመን እንዲሆን በየቀኑ የሚቀጠሩ ጉዳዮች መጠንና መስራት ከሚቻል አቅም በላይ ወይም በታች መሆን የለበትም፣
6. ለፍ/ቤት ችሎት ድርጊቶች ክንወን የሚሰጥ ቀነ ቀጠሮ ተለዋጭ ቀጠሮ ጥያቄን በማያስከትል ሁኔታ ይሰጣል፣
7. ቅድመ ሙግት መስማት፣ ሙግት መስማት እና ፍርድ መስጠት ድርጊቶች ክንውን ሳይቀላቀሉ ተለያይተተው የሚቀጠሩ ይሆናል፡፡

8. ከላይ በተራ ቁጥር 7 ስር ከተጠቀሰው ውጭ እንዲከናወኑ ወይም እንዲፈጸሙ የታዘዙ ድርጊቶች ውጤት ለመጠበቅ የሚቀጠሩ ጉዳዮች ሳይበታተኑ አንድ ላይ የሚቀጠሩ ይሆናል፡፡

13. <u>ተለዋጭ ቀጠሮ አሰጣጥ</u>

በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተለዋጭ ቀጠሮ ፍላጎት መኖሩ ወይም ጥያቄው መቅረቡ ብቻውን ተለዋጭ ቀጠሮ አያሰጥም፣ ነገር ግን ተለዋጭ ቀጠሮ ለመስጠት ወይም ለመከለከል የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግንዛቤ የሚገቡ ይሆናል፣

1. ለተለዋጭ ቀጠሮ ምክንያት ተደርጎ የቀረበው ስጋት ወይም አለመመቸት በሌላ ሁኔታ መፍታት የማይቻል መሆኑን በመመዘን፣
2. ተለዋጭ ቀጠሮ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት ለጥያቄው ምክንያት የሆነውን ነገር ለመቅረፍ ወይም ለመፍታት  የተደረገ ጥረት ስለመኖሩ በማረጋገጥ፣
3. ተለዋጭ ቀጠሮ የተጠየቀበት ጉዳይ በሂደት ላይ የቆየበት ጊዜ መጠን ከግንዛቤ በመውሰድ፣
4. ከዚህ ቀደም ተለዋጭ ቀጠሮ ያልተጠየቀ መሆኑ እንዲሁም ተጠይቆ የተፈቀደ ወይም ያልተፈቀደ ስለ መሆኑ በመለየት፣
5. በተለዋጭ ቀጠሮ ምክንያት የጉዳዩ መጓተት ሌላው ባለጉዳይ ተገቢ በሆነ ጊዜ ገደብ ውስጥ የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብት ላይ ተፅእኖ የማይፈጥር መሆኑን ከግምት በማስገባት፣
6. የሚሰጠው ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ ጉዳዩ በተቀመጠለት ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት እንዳያገኝ ለማድረግ ያለው አስተዋጾ ከግምት በማስገባት፣
7. ከተራ ቁጥር 1-7 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው ሌላ አሳማኝ የሆነ ምክንያት መኖሩን ዳኛ የተረዳ እንደሆነ ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ መስጠት የሚከለክል አይደለም፣

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር እና የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

14. <u>የጉዳዮች ሂደት ደረጃ የመከታተል መርህ</u>

1. የጉዳዮች ሂደት ደረጃ እያደገ እንዲሄድ መዝገብ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ባለማቋረጥ ቁጥጥር የማድረግ፤

2. በእያንዳንዱ ጉዳይ ውስጥ የፍርድ ቤት ችሎት ድርጊቶች እየተፈጸሙ (እየተከናወኑ) እንዲጓዙ የመቆጣጠር፣ የመከታተልና የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ፣
3. የጉዳዮች ሂደት ከነበረበት ወይም ድርጊት ደረጃ ወደሚቀጥለው ሂደት ወይም ድርጊት ደረጃ እንዲሻገር ያለማቋረጥ ቁጥጥር የማድረግ፤

15. <u>የፕሬዚዳንት ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌሎች ህጎች ለፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት፡-

1. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር አተገባበር በመከታተል፣ በመቆጣጠርና አፈፃፀም እንዲላክ በማድረግ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወስድም ያደረጋል፣
2. ጉዳዮች በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያላገኙበትን ውስጣዊ እና ውጫዊ ምክንያቶችን በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ የሚያመላክት የዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወስድም ያደርጋል፣
3. ሬጅስትራሮች፣የጉዳዮች ፍሰት አስተዳዳር ሙያተኞች፣ረዳት ዳኞች፣የመዝግብት መረጃ አያያዝ አስተዳዳሪ እና ሌሎች ሠራተኞች ለዚህ መመሪያ ተግባራዊነት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በአግባቡ ማከናወናቸውን ያረጋግጣል፣
4. በዚህ መመሪያ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ውጤታማ እንዲሆኑ የእውቀት፣ የክህሎት እና ሌሎች ክፍተቶችን ለመሙላት ስልጠናና መልካም ተሞክሮ መቅሰም ተግባራት እንዲከናወኑ ያደረጋል፣
5. ለጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ስኬታማነት ምቹ የችሎት አደረጃጀት፣ የሰው ሀይል ስምሪትና የጉዳዮች ድልድል እንዲኖር ያደርጋል፤ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ሁሉ ያከናውናል፡፡
6. ለጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ስኬታማነት ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ያከናውናል፡፡

16. <u>ሰብሳቢ ዳኛ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የችሎት ሰብሳቢ ዳኛ በሌሎች ህጎችና መመሪያዎች ያለው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ተግባራዊነት የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል ፡-

1. በችሎቱ የሚከናወኑ የዳኝነት ተግባራት ቀልጣፋ፣ ተገማችና ተደራሽ እየሆነ እንዲሄድ የሚያደርጉ አስተዳደራዊ ተግባራትን የማከናወን፣
2. ጉዳዮች በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት እንዲያገኙ በቅርበት የጉዳዮችን ሂደት ይቆጣጠራል፣ የፈጻጸም ሁኔታውን በመከታተል ሪፖርት የማቅረብ፤ የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ፣
3. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ጠንካራ ጎኖችን ማጠናከር፣ ውስንነቶችን በመለየት መሻሻልና አዲስ መካተት ያለባቸውን ሀሳቦች የማመንጨት ተግባር የማከናወን፣
4. የቀጠሮ አሰጣጥ ሁኔታ፣ ተለዋጭ ቀጠሮ እና ተጨማሪ ተለዋጭ ቀጠሮ የጉዳዮችን ሂደት እንዳያጓትት የሚያግዝ ተግባር የማከናወን፣
5. በተቀመጠው ጊዜ ገደብ በውስጥ ለጉዳዮች እልባት ከመስጠት ረገድ ያለውን አፈጻጸም ለችሎቱ ዳኞች የማሳወቅ፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረግ፣
6. ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ወይም ባለሙያዎች ለዚህ መመሪያ ተግባራዊነት የበኩላቸውን እንዲወጡ የማድረግ፤
7. ጉዳዩች በተቀመጠላቸው መቋጫ ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት እንዳያገኙ ያደረጉ ውስጣዊ እና ውጫዊ ምክንያቶችን በመለየት ከችሎቱ ዳኞች ጋር በመወያየት የተደረሰበትን መግባባት መሠረት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ወይም እንዲወሰድ ለሚመከተው አካል የማሳወቅ፤

17.<u>የዳኞች ተግባርና ኃላፊነት</u>

ለጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ወይም ሂደት ስኬታማነት ዳኞች የሚመለከተው ተግባርና ሀላፊነት ይኖራቸዋል፡-

1. ጉዳዮች እንደየመደባቸው እና ተናጠል ባህሪያቸው የሂደት ደረጃቸው እያደገ እንዲሄድ ባለማቋረጥ የመከታተል፤ የሂደት ደረጃቸው ወይም እድገቱ አጥጋቢ ባልሆነበት ጊዜ ጣልቃ በመግባት አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ የመውሰድ፤
2. ጉዳዮች በጊዜ ገደባቸው ውስጥ እልባት እንዲያገኙ የማድረግ፤
3. የፍ/ቤት ችሎት ድርጊት (ክንውን) ለጉዳዮች ሂደት ደረጃ እድገትና ለባለጉዳዮች ጊዜና ወጪ በመቆጠብ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤

4. እንዲከናወኑ በሚታዘዙ ድርጊቶች መካከል ያለው የጊዜ መጠን የጉዳዮች ሂደትና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ በሚያሳካ ሁኔታ የመወሰን፣
5. ጉዳዮች እንደየተናጠል አይነታቸውና ባህሪያቸው ተመጣጣኝና ተገቢ ትኩረት በመስጠት የጉዳዩ ሂደት እንዲፋጠን የማድረግ፣
6. ጉዳዮችን እንደየተናጠል ባህሪያቸው በተቀመጠላቸው ቀነ ገደብ ውስጥ ቀላል፣መካከለኛ እና ውስብስብ መሆናቸውን በመለየት መምራት፤
7. ተከራካሪ ወገኖች ወይም ባለጉዳዮች አለመግባባታቸውን በራሳቸው ስምምነት እንዲፈቱ የማድረግ፣
8. በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰሩ ስራዎችን አፈፃፀም በመደበኛነት ለሚመለከተው ሪፖርት የማድረግ፣
9. በቅድመ ሙግት መስማት ሂደትና ተግባር ለሚከናወኑ የድርጊቶች ክንውን ተጨባጭ ቀጠሮ የመስጠት ፤
10. ለሙግት መስማት ሂደትና ተግባር ለሚከናወኑ የድርጊቶች ክንከውን ተጨባጭ ቀጠሮ የመስጠት
11. ለእያንዳንዱ የፍ/ቤት ችሎት ድርጊቶች በተገቢ ሁኔታ መከናወን ወይም መፈጸም በቂ የሆነ ዝግጅት የማድረግ
12. ለመጀመሪያ ክስ መስማት ተግባር ተከራካሪ ወገኖች በቂ ዝግጅት አድርገው እንዲቀርቡ ማሳሰብና በመጀመሪያ ክስ መስማት ሂደት ደረጃ ስር ያሉ ተግባራት ተጠቃለው መከናወናቸውን የማረጋገጥ፤
13. የመጀመሪያ ክስ መስማት ተግባር እንዲሁም ክርክርና ምስክሮችን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ ከመስጠቱ በፊት እንደየአግባብነቱ፡-
    - ሀ/ የቋንቋ ወይም የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ፍላጎት መኖር እና አለመኖሩን ማረጋገጥ፣
    - ለ/ የችሎት ሂደት መቅረፀ ድምፅ ዝግጁ መሆኑንና አለመሆኑን ማረጋገጥ፣
    - ሐ/ ተከራካሪ ወገኖች ምስክሮቻቸውን አሟልተው ማቅረብ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡

14. የጽሁፍ ክርክር ቅብብሎሽ መጠናቀቅን ተከትሎ ለሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት እንደየቅደም ተከተላቸው የተከራካሪ ወገኖችን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የክዋኔ መርሀ ግብር በማዘጋጀት በዚያው መሰረት ድርጊቶች ሂደታቸው ተጠናቆ እልባት እንዲያገኙ የማድረግ፤
15. በተቻለ መጠን ከአንድ በላይ የሆኑ ድርጊቶች አንድ ላይ በማሰባሰብ በአንድ ቀጠሮ እንዲከናወኑ የማድረግ፤

## 18.<u>የተከራካሪ ወገኖች ተግባርና ኃላፊነት</u>

ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ተከራካሪ ወገኖች፡-

1. በእያንዳንዱ ጉዳይ ሂደት ደረጃ እና በየቀጠሮ ተከናውኖ መጠናቀቅ የሚገባቸው ተግባራትን በጥብቅ ዲሲፕሊን የማከናወን፤
2. የጉዳዮች ሂደት ተጠናቆ እልባት እንዲያገኙ የሚያስችሉ ተግባራትን በተሟላ ስነምግባር የማከናወን፤
3. የጉዳዮች ሂደትና እልባት መስጫ ጊዜን ለማንተት በማሰብ ተገቢ ያልሆነ አቤቱታ ያለማቅረብ፣
4. የፍ/ቤት ትእዛዞችን የማክበር እና የመፈጸም፤

## 19.<u>የሬጅስትራሮች ተግባርና ኃላፊነት</u>

ሬጅስትራሮች በህግና አሰራር የተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. መዝገብ እንዲከፈት የቀረበላቸውን ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት በየትኛው መደብ ስር እንደሚመደቡ የመለየት እና በተዘረጋው ስርአት መሰረት ለሚመለከተው ችሎት የመመደብ፤
2. ከላይ በቁጥር 1 ስር በተገለጸው መሰረት ተለይተው የተመደቡ ጉዳዮችን በዚህ በመመሪያው መሰረት እልባት የሚያገኙበትን የጊዜ ገደብ ለተከራካሪ ወገኖች የማሳወቅ፤
3. ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት እንዲያከናውኑ የሚጠበቅባቸውን ተያያዥ ተግባራት በተሟላ ስነምግባር ተገቢውን የማከናወን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

## 20. <u>የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የስራ ክፍል በህግ አግባብ እና በአሰራር ያለው ኃላፊነት እና ተግባር እንተደጠበቀ ሆኖ፡-

   ሀ/ መዝገብ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ እልባት እስከሚያገኝበት ቀን ድረስ ያለው የጉዳዮችን እንቅስቃሴ መሰረት ያደረገ መረጃ የመያዝ እና የማስተዳደር፣

   ለ/ የጉዳዮች ሂደት መቋጫ እና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ አፈጻጸም መለኪያ አመላካቾችን በመጠቀም የአፈጻጸም ደረጃን በመለካት ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፣

   ሐ/ የጉዳዮች ሂደት ደረጃ ሁኔታ እና ተያያዥ ተግራት አፈጻጸምን ማወቅ የሚያስችል በስታትስቲክስ የተደገፈ መረጃ ለሚመከተው አካል የማቅረብ፣

   መ/ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ጠንካራ ጎኖችን ለማጠናከር እና ውስንነቶችን በመለየት መሻሻልና አዲስ መካተት ያለባቸውን ሀሳቦች የማመንጨት ተግባር የማከናወን፣

   ሠ/ ሌሎች የጉዳዮች ፍሰት እተዳደርን ስኬታማ እንዲሆን የሚያደርጉ ተግባራትን የማከናወን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

2. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ክፍል በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ይደራጃል፡፡

21.<u>የፍ/ቤት ተቋማዊ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት</u>

1. ማናቸውም ፍርድ ቤት የሚከተሉትን ማከናወን ይኖርበታል፡-

   ሀ/ ዳኝነት የተጠየቀባቸው ጉዳዮች በዚህ መመሪያ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት እንዲያገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግ፣

   ለ/ የጉዳዩች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ በኤሌክትሮኒክስና ህትመት ሚዲያዎች ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ፣

   ሐ/ በአጠቃላይ ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያገኙ ጉዳዮች፣ እልባት ያላገኙ ጉዳዮች እና የጉዳዮች ማጥራት ምጣኔ አፈጻጸም በመለካት ባለማቋረጥ ለህዝብ የማሳወቅ፣

   መ/ የጉዳዮች ሂደት መቋጫ እና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ አፈጻጸም ማሻሻል የሚያስችል አግባብነት ያለው እርምጃ የመውሰድ፤

ሠ/ ከጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መርሆች ጋር በተጣጣመ አኳኋን አፈጻጸምን ስኬታማ ማድረግ የሚያስችል ስልት ተግበራዊ የማድረግ፣ አስፈላጊም ሲሆን ለመመሪያው ተግባራዊነት የሚያግዝ ማኑዋል የማዘጋጀት፤

ረ/ በተቀመጠላቸው ጠቅላላ የጊዜ ገድብ ውስጥ እልባት ያላገኙ ውዝፍ መዝገቦችን ለማጥራት የሚያስችል ስልት እና አሰራር ተግባራዊ የማድረግ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን አለመፈጸም ተቋማዊ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ ለተጠያቂነቱ መረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የጉዳዮች እልባት የመስጫ ጊዜ ገደብ፣ ተጠባቂ ግብ እና የጊዜ ገደብ የአፈጻጸም መለኪያዎች

### 22.የጉዳዮች መደብ፣ እልባት የመስጫ ጊዜ ገደብና ተጠባቂ ግብ

1. በእያንዳንዱ ፍ/ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች በየመደባቸው ተለይተው ለእያንዳንዱ ጉዳይ የእልባት የመስጫ ጊዜ ገደብ እና ተጠባቂ ግብ እንዲኖረው ተደርጓል፤
2. በእያንዳንዱ ፍ/ቤት የሚታዩ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ አባሪ አንድ በተያያዘው ሰንጠረዥ መሰረት ለጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ በተቀመጠው መሰረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡
3. ዳኞች በዚህ መመሪያ አባሪ አንድ በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው አኳኋን የጉዳዮች ሂደት መቋጫና ተጠባቂ ግብ መሰረት ጉዳዮች እልባት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 23.የጊዜ ገደብ አፈጻጸም መለኪያ አመላካቾች

1. በአጠቃላይ ጊዜ ገደብ ውስጥ የተለያዩ ጊዜ ገደቦች እንዲኖሩ የተደረገ ሲሆን፤ መነሻ ጠቅላላ ጊዜ ገደብ፣ መካከለኛ ጠቅላላ ጊዜ ገደብ እና አጠቃላይ ጊዜ ገደብ ተብለው ተለያይተው ተቀምጠዋል፡፡
2. ለጊዜ ገደብ ስሌት ሲባል የጊዜ ገደብ መቁጠሪያ መነሻ መዝገብ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ሲሆን ፍጻሜው ደግሞ ጉዳዩ እልባት ያገኘበት ቀን ይሆናል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር 2 ስር የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር ችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮች ጊዜ ገደብ መቁጠሪያ መነሻ ያስቀርባል ከተባለበት ቀን የሚጀመር ይሆናል፡፡

4. የጊዜ ገደብ አፈጻጸም ዋና አመላካቾች እና መለኪያ መንገዶች የጉዳዮች የማጥራት ምጣኔ በመቶኛ፣ እልባት የተሰጠበት ጊዜ በመቶኛ እና የጉዳዮች እድሜ በመቶኛ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ የጊዜ ገደብ አፈጻጸም ዋና አመላካቾች እና መለኪያዎች ስሌት በዚህ መመሪያ በአባሪ 2 በተቀመጠው መሰረት የሚሰላ ሲሆን የዚህ አፈጻጸም መከታተያና ሪፖርት ማድረጊያ ፎርም በአባሪ 3 በተገለጸው መሰረት ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል፡፡ ሆኖም ይህ ፎርም በየጊዜው እየታየ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 24. ስለመተባበር

ተከራካሪ ወገኖች ለጉዳዮች ሂደት ድርጊቶች ክንውን በቂ ዝግጅት በማድረግ፤ የጉዳዮች ሂደት እና እልባት መስጫ ጊዜ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚበቅባቸውን ሁሉ በማከናወን የመተባበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### 25. ፍርድ ቤት መር አስማሚነት

1. ሙግት መስማት ሂደት ከመጀመሩ በፊት በማንኛውም ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በራሳቸው በስምምነት እንዲቋጩ ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡
2. የማስማማት ሂደቱ እንዲጀመር ዳኛ ካዘዘበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ዳኞች በቂ ምክንያት መኖሩን ከተረዱ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከ20 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ማራዘም ይችላሉ፡፡
3. ከላይ ከቁጥር 1 እስከ 2 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት መር አስማሚነት ሂደት የሚመራው ለዚህ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

### 26. የተከለከሉ ተግባራት

1. ጉዳዮች ቀጠሮ ሳይሰጣቸው እና መረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ውስጥ ሳይመዘገቡ በእንጥልጥል ችሎቶች፣ ዳኞች ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው የአስተዳደር ሰራተኞች ዘንድ እንዲቆዩ ማድረግ፣
2. ባለጉዳዮች ለፍርድ ቤት ያላቸውን ክብር እና አመኔታ የሚጎዳ ድርጊቶችን መፈፀም፣
3. ለጉዳዮች ተደጋጋሚ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጥ አስተዋጾ ማድረግ፣

4. በጉዳዮች ሂደት ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት በቂ ከሆነ ጊዜ በላይ ረጅም ቀነ ቀጠሮ መስጠት፣
5. የምርመራ እና የእለት መዝገቦች ተገቢ በሆነ ጊዜ ለዳኞች ወይም ለችሎቶች አሟልቶ ባለማቅረብ ባለጉዳዮችን ለእንግልት እና ለተለዋጭ ቀጠሮ መዳረግ፣

27.**<u>መመሪያ ስለማሻሻል</u>**

ይህ መመሪያ በማንኛውም ጊዜ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡

28.**<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የሁለት ወር የዝግጅት ጊዜ ሊኖረው ይችላል፡፡

**መዓዛ አሸናፊ**

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት**

<u>አባሪ - 1</u>

# የፌዴራል ፍ/ቤቶች የጉዳዮች እልባት መስጫ ጊዜ ገደብና ተጠባቂ ግብ

## 1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

| ተ.ቁ | ፍ/ቤት | ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት | የጉዳዮች ሂደት ጅማሬና ፍጻሜ | የጉዳዮች መደብ (አይነት) | የጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ እና ተጠባቂ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 85% መነሻ ጠቅላላ ጊዜ | 95% መካከለኛ ጠቅላላ ጊዜ | 100% አጠቃላይ ጊዜ ገደብ |
| 1 | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | ለፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት | መዝገብ ከተከፈተበት ጀምሮ እልባት እስከተሰጠበት ቀን ድረስ | - ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 210 ቀናት | 270 ቀናት |
| | | | | - ውርስን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የቤተሰብ ጉዳዮችና የባልና ሚስት ፍቺ እና የፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 180 ቀናት | 240 ቀናት |
| | | | | - የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>-የንግድ ውድድርና ሸማቾች መብትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 180 ቀናት | 240 ቀናት |
| | | | | - የንብረት ባለቤትነት ክርክር ጉዳዮች<br>- ከሁከት፣ ይዞታ እና ከሊዝ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 180 ቀናት | 210 ቀናት |
| | | | | - ከአሰሪና ሰራተኞች፣ከመንግስት ሰራተኞች እና ሌሎች የስራ ግንኙነቶችን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- ከህጻናት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች (ቀለብ እና ጉዲፈቻ)<br>- ከፍርድ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 40 ቀናት | 50 ቀናት | 60 ቀናት |
| | | | | ሌሎች በግልጽ ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 180 ቀናት | 210 ቀናት |

| ተ.ቁ | ፍ/ቤት | ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት | የጉዳዮች ሂደት ጅማሮና ፍጻመ | የጉዳዮች መደብ (አይነት) | የጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ እና ተጠባቂ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 85% መነሻ ጠቅላላይ ጊዜ | 95% መካከለኛ ጠቅላላ ጊዜ | 100% አጠቃላይ ጊዜ ገደብ |
| 3 | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | ለሰበር ችሎት | ጉዳዩ ያስቀርባል ከተባለበት ቀን ጀምሮ እልባት እስከተሰጠበት ቀን ድረስ | -ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>-ከውል ውጭ ሀኃላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 180 ቀናት | 240 ቀናት | 300 ቀናት |
| | | | | -ውርስን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>-የቤተሰብ ጉዳዮችና ከባልና ሚስት ፍቺና የፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 180 ቀናት | 210 ቀናት | 270 ቀናት |
| | | | | -የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>-የንግድ ውድድርና ሸማቾች መብትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 180 ቀናት | 210 ቀናት |
| | | | | -የንብረት ክርክር ጉዳዮች<br>-ከሁከት፣ ይዞታና ሊዝ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 150 ቀናት | 210 ቀናት | 240 ቀናት |
| | | | | -ከአሰሪና ሰራተኞች፣ከመንግስት ሰራተኞች እና ሌሎች የስራ ግንኙነቶችን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>-ከህጻናት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች (ቀለብ እና ጉዲፍቻ)<br>- ከፍርድ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | ---------- | --------- | 60 ቀናት |
| | | | | ሌሎች በግልጽ ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 150 ቀናት | 210 ቀናት |

| ተ. ቁ | ፍ/ቤት | ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት | የጉዳዮች ሂደት ጅማሬና ፍጻሜ | የጉዳዮች መደብ (አይነት) | የጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ እና ተጠባቂ ግብ | | |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| | | | | | 85% መነሻ ጠቅላላ ጊዜ | 95% መካከለኛ ጠቅላላ ጊዜ | 100% አጠቃላይ ጊዜ ገደብ |
| 2 | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | ሰበር አጣሪ ችሎት | መዝገቡ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም እስከተባለበት ቀን ድረስ | - ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | --------- | ------- | 90 ቀናት |
| | | | | - ውርስን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የቤተሰብ ጉዳዮች እና የባልና ሚስት ፍቺና ከፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | --------- | ------- | 90 ቀናት |
| | | | | - የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የንግድ ውድድርና ሸማቾች መብትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | -- ----- | ------ | 90 ቀናት |
| | | | | - የንብረት ክርክር ጉዳዮች<br>- ከሁከት፣ ከይዞታና ከሊዝ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | --------- | ------- | 90 ቀናት |
| | | | | - ከአሰሪና ሰራተኞች፣ከመንግስት ሰራተኞች እና ሌሎች የስራ ግንኙነቶችን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የባልና ሚስት ፍቺ ጉዳዮች<br>- ከህጻናት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች (ቀለብ እና ጉዲፍቻ)<br>- ከፍርድ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | ---------- | --------- | 60 ቀናት |
| | | | | ሌሎች በግልጽ ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | ------- | ------ | 90 ቀናት |

## 2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

| ተ.ቁ | ፍ/ቤት | ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት | የጉዳዮች ሂደት ጅማሮና ፍጻመ | የጉዳዮች መደብ (አይነት) | የጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ እና ተጠባቂ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 85% መነሻ ጠቅላላይ ጊዜ | 95% መካከለኛ ጠቅላላ ጊዜ | 100% አጠቃላይ ጊዜ ገደብ |
| 1 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት | ለቀጥታ ክስ ችሎት | መዝገብ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ እልባት እስከሚሰጠበት ቀን ድረስ | ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 210 ቀናት | 270 ቀናት | 365 ቀናት |
| | | | | የኮንስትራክሽን ጉዳዮች | 210 ቀናት | 365 ቀናት | 425 ቀናት |
| | | | | ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 270 ቀናት | 365 ቀናት | 485 ቀናት |
| | | | | -የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>-ከፍቺ ውጤት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች<br>-ከውርስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 180 ቀናት | 270 ቀናት | 365 ቀናት |
| | | | | የሁከት ይወገድ ጉዳዮች | 90 ቀናት | 105 ቀናት | 120 ቀናት |
| | | | | ከይዞታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 300 ቀናት | 425 ቀናት | 485 ቀናት |
| | | | | ሌሎች ያልተገለጹ ጉዳዮች | 180 ቀናት | 270 ቀናት | 365 ቀናት |
| | | | | ከፍርድ ማስፈጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 90 ቀናት | 180 ቀናት | 365 ቀናት |

| ተ.ቁ | ፍ/ቤት | ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት | የጉዳዮች ሂደት ጅማሮና ፍጻመ | የጉዳዮች መደብ (አይነት) | የጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ እና ተጠባቂ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 85% መነሻ ጠቅላላይ ጊዜ | 95% መካከለኛ ጠቅላላ ጊዜ | 100% አጠቃላይ ጊዜ ገደብ |
| 2 | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት | ለፍትሐብሔር ይግባኝ ችሎት | መዝገቡ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ እልባት እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ | - ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 180 ቀናት | 210 ቀናት |
| | | | | ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 90 ቀናት | 180 ቀናት | 210 ቀናት |
| | | | | -ከፍቺና ፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች<br>-በአስተዳደር መ/ቤት እና ሌሎች አካላት ከሚሰጡ ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮች<br>-በአስተዳደር መ/ቤት እና ሌሎች አካላት ከሚሰጡ ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮች<br>-ከአስተዳደር ህግ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 150 ቀናት | 180 ቀናት |
| | | | | -የስራ ክርክር ጉዳዮች<br>-ከፍርድ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 30 ቀናት | 45 ቀናት | 60 ቀናት |
| | | | | ከሁከትና ይዞታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 90 ቀናት | 105 ቀናት | 120 ቀናት |
| | | | | ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 150 ቀናት | 180 ቀናት |

## 3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

| ተ.ቁ | ፍ/ቤት | ጉዳዩ የቀረበለት ችሎት | የጉዳዮች ሂደት ጅማሮና ፍጻሜ | የጉዳዮች መደብ (አይነት) | የጉዳዮች ሂደት መቋጫና እልባት መስጫ ጊዜ ገደብ እና ተጠባቂ ግብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 85% መነሻ ጠቅላላይ ጊዜ | 95% መካከለኛ ጠቅላላ ጊዜ | 100% አጠቃላይ ጊዜ ገደብ |
| 1 | የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት | የመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ተጠይቆባቸው ለችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮች | መዝገብ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ እልባት እስከተሰጠበት ቀን ድረስ | ቀለብ ይወሰን (ይሻሻል) | 10ቀናት | 20ቀናት | 30 ቀናት |
| | | | | ባልና ሚስት ፍቺ | 90 ቀናት | 150 ቀናት | 180 ቀናት |
| | | | | የባልና ሚስት ንብረት ክርክር | 90 ቀናት | 270 ቀናት | 300 ቀናት |
| | | | | ልጅነት ወይም አባትነት ማረጋገጥ የሚቀርቡ ጉዳዮች | በ10 ቀናት | 30 ቀናት | 50 ቀናት |
| | | | | የመካድ ክስ (ልጅነት፣አባትነት፣ሚስትነት፣ባልነት ውሳኔ ይሰረዝ) | 90 ቀናት | 135 ቀናት | 180 ቀናት |
| | | | | ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 180 ቀናት | 280 ቀናት | 300 ቀናት |
| | | | | ከውል ውጪ ያለ ግንኙነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 180 ቀናት | 240 ቀናት | 350 ቀናት |
| | | | | ይዞታ፤ ሁከት እና የቤት ኪራይ ውልን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች | 90 ቀናት | 105 ቀናት | 120 ቀናት |
| | | | | አጭር ስነ-ስርዓት የሚታዩ ጉዳዮች | 60 ቀናት | 75 ቀናት | 90 ቀናት |
| | | | | ባንክና ኢንሹራንስ ጉዳዮች | 90 ቀናት | 150 ቀናት | 180 ቀናት |
| | | | | የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | 150 ቀናት | 240 ቀናት | 300 ቀናት |
| | | | | ውርስ ሃብት ለማጣራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 120 ቀናት | 150 ቀናት | 210 ቀናት |
| | | | | ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 90 ቀናት | 150 ቀናት | 180 ቀናት |
| | | | | ከስራ ክርክር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | 40 ቀናት | 50 ቀናት | 60 ቀናት |
| | | | | የፍርድ ማስፈጸም ጉዳዮች | 90 ቀናት | 180 ቀናት | 365 ቀናት |

## አባሪ -2
## የአፈጻጸም መለኪያ አመላካቾች ትርጉም እና ስሌት

### 1. ጉዳዮችን የማጥራት ምጣኔ፡-

ጉዳዮችን የማጥራት ምጣኔ አፈጻጸም መመዘን ያስፈልጋል፡፡ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያገኙ ጉዳዮች እና አዲስ የተከፈቱ መዝገቦች መመጣጠን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያገኙ ጉዳዮች እና አዲስ የተከፈቱ መዝገቦች ካልተመጣኑ ወይም እልባት ያገኙ ጉዳዮች አዲስ ከተከፈቱት ጉዳዮች በመጠን ያነሰ ከሆነ የሚወዘፉ ጉዳዮች እየተፈጠሩ እና መጠናቸው እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የጉዳዮች የማጥራት ምጣኔ ስሌት እንደሚከተለው

$$\text{ጉዳዮችን የማጥራት ምጣኔ በመቶኛ (\%)} = \frac{\text{በተወሰነ ጊዜ ውስጥ (አንድ አመት) እልባት ያገኙ ጉዳዮች}}{\text{በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ (አንድ አመት) አዲስ የተከፈቱ መዝገቦች በጠቅላላው}} \times 100$$

### 2. እልባት የተሰጠበት ጊዜ ፡-

በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያገኙ ጉዳዮችን አፈጻጸም በፐርሰንት ለመለየት በሚከተለው ሁኔታ ስሌት እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

$$\text{እልባት የተሰጠበት ጊዜ በመቶኛ} = \frac{\text{በቀነ ገደቡ እልባት ያገኙ ጉዳዮች መጠን}}{\text{እልባት ያገኙ ጉዳዮች መጠን በጠቅላላው}} \text{X } 100$$

### 3. የጉዳዮች እድሜ፡-

በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ሳያገኙ ቀርተው ሂደታቸው የቀጠሉ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው፡፡ በሂደት ላይ ያሉ ጉዳዮች እድሜ ምዘና መዝገብ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ እልባት ማግኘት እስከነበረባቸው ቀን ድረስ ይሆናል፡፡ ስሌቱም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

$$\text{የጉዳዮች እድሜ በመቶኛ} = \frac{\text{በጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያላገኙ እና እየታዩ የሚገኙ ጉዳዮች}}{\text{እየታዩ የሚገኙ ጉዳዮች በጠቅላላው}} \text{X } 100$$

# <u>አባሪ - 3</u>
# <u>የአፈጻጸም መከታተያና ሪፖርት ማድረጊያ ፎርም</u>

**1.** በሰበር ችሎት በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት <u>ያገኙ እና ያላገኙ</u> ጉዳዮች ዝርዝር አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርም

| መንገድ (Track) | የጉዳዮች አይነት | ጊዜ ገደብ | እልባት ያገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም በመቶኛ (%) | እልባት ያላገኙ ጉዳዮች በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 1 | - ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ240 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ300 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ300 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 2 | - ውርስን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የቤተሰብ ጉዳዮችና ከባልና ሚስት ፍቺና የፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀናትውስጥ | | |
| | | በ270 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ270 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 3 | - የንብረት ክርክር፣ኪራይ፣ ሊዝ፣ ሁከትና ይዞታ ጉዳዮች<br>- የንብረት ክርክር ጉዳዮች | በ150 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ210ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ240 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ240 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 4 | - የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የንግድ ውድድርና ሸማቾች መብትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀን ውስጥ | | |
| | | *ከ210 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 5 | - ከአፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች<br>- ጉዳዮች፣አሰሪና ሰራተኞች፣የመንግስት ሰራተኞች ጉዳይ እና ሌሎች የስራ ግንኙነት መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የህጻናት ጉዳይ (ቀለብ እና ጉድፈቻ)፣ | በ60 ቀን ውስጥ | | |
| | | *ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 6 | ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | በ120 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ150 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ210 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |

**2.** አጣሪ ችሎት በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት <u>ያገኙ እና ያላገኙ</u> ጉዳዮች ዝርዝር

| መንገድ (Track) | የጉዳዮች አይነት | ጊዜ ገደብ | እልባት ያገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም በመቶኛ (%) | እልባት ያላገኙ ጉዳዮች በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 1 | ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 2 | ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 3 | ውርስን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 4 | የቤተሰብ ጉዳዮችና ከባልና ሚስት ፍቺና የፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 5 | የንብረት ክርክር፣ኪራይ፣ ሊዝ፣ ሁከትና ይዞታ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 6 | የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 7 | ከአፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ 60 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 8 | ጉዳዮች፣አሰሪና ሰራተኞች፣የመንግስት ሰራተኞች ጉዳይ እና ሌሎች የስራ ግንኙነት መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ 60 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 9 | የህጻናት ጉዳይ (ቀለብ እና ጉድፈቻ)፣ | በ 60 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 10 | ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |

## 3. በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት <u>ያገኙ እና ያላገኙ ይግባኝ</u> ጉዳዮች ዝርዝር አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርም

| መንገድ (Track) | የጉዳዮች አይነት | ጊዜ ገደብ | እልባት ያገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም በመቶኛ (%) | እልባት ያላገኙ ጉዳዮች በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 1 | ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ120 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ270 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ270 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 2 | ውርስን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ240 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ240 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 3 | የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ240 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ240 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 4 | የንብረት ክርክር፣ ኪራይ፣ ሊዝ፣ ሁከትና ይዞታ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ210 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 5 | የቤተሰብ ጉዳዮችና የባልና ሚስት ፍቺና የፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ240 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ240 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 6 | ከውል ውጭ ሀላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ270 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ270 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 7 | ከአፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ60 ቀን ውስጥ | | |
| | | | | |
| | | ***ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 8 | - የህጻናት ጉዳይ (ቀለብ እና ጉዲፈቻ)፣<br>- አሠሪና ሠራተኛ፣የመንግስት ሰራተኞች ጉዳይ እና ሌሎች የስራ ግንኙነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ 40 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ50ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ60 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| | | **በ210** ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ210 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |

## 4. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት ያገኙ እና ያላገኙ ጉዳዮች ዝርዝር አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርም

| መንገድ (Track) | የጉዳዮች አይነት | ጊዜ ገደብ | እልባት ያገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም በመቶኛ (%) | እልባት ያላገኙ ጉዳዮች በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 1 | ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ210 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ270 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ365 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ365 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 2 | ከውል ውጭ ሀላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ270 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ365 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ485 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ485 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 3 | የኮንስትራክሽን ጉዳዮች | በ210 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ365 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ425 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ425 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 4 | የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>ከፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች<br>የውርስ ጉዳዮች | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ270 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ365 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ365 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 5 | የሁከት ይወገድ ጉዳዮች | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ105 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ120 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ120 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 6 | ከይዞታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ300 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ425 ቀናት ውስጥ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በ485 ቀናት ውስጥ | | |
| | | | ***ከ485 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | |
| መንገድ 7 | የፍርድ አፈጻጸም ጉዳዮች | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ365 ቀናት ውስጥ | | |
| | | | ***ከ365 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | |
| መንገድ 8 | ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ270 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ365 ቀናት ውስጥ | | |
| | | | ***ከ365 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | |

5. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት **ያገኙ እና ያላገኙ** ጉዳዮች ዝርዝር አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርም

| **መንገድ** (Track) | **የጉዳዮች አይነት** | **ጊዜ ገደብ** | **እልባት ያገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም በመቶኛ (%)** | **እልባት ያላገኙ ጉዳዮች በመቶኛ (%)** |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 1 | - ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች<br>- የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ210 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 2 | ከውል ውጭ ሀላፊነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ90 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ210 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 3 | -ከፍቺና ፍቺ ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች<br>-በአስተዳደር መ/ቤት እና ሌሎች አካላት ከሚሰጡ ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮች<br>-በአስተዳደር መ/ቤት እና ሌሎች አካላት ከሚሰጡ ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮች<br>-ከአስተዳደር ህግ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ150 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ180 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ 4 | -የስራ ክርክር ጉዳዮች<br>- ከፍርድ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ30 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ45 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ60 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ 5 | የሁከትና ይዞታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ90 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ105 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ120 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ 6 | ሌሎች ያልተጠቀሱ ጉዳዮች | በ120 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ150 ቀን ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀን ውስጥ | | |
| | | ***ከ180 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |

6. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ እልባት <u>**ያገኙ እና ያላገኙ**</u> ጉዳዮች ዝርዝር አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርም

| መንገድ (Track) | የጉዳዮች አይነት | ጊዜ ገደብ | እልባት ያገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም በመቶኛ (%) | እልባት ያላገኙ ጉዳዮች በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 1 | ቀለብ ይወሰን (ይሻሻል) | በ10 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ20 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ30 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ30 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 2 | የባልና ሚስት ፍቺ | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ150 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ180 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 3 | የባልና ሚስት ንብረት ክርክር | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ270 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ300 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ300 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 4 | ልጅነት ወይም አባትነት ማረጋገጥ የሚቀርቡ ጉዳዮች | በ10 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ30 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ50 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ50 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |
| መንገድ - 5 | የመካድ ክስ (ልጅነት፣አባትነት፣ሚስትነት፣ባልነት ውሳኔ ይሰረዝ) | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ135 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ180 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |

| መንገድ (Track) | የጉዳዮች አይነት | ጊዜገደብ | እልባት ያገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም በመቶኛ (%) | እልባት ያላገኙ ጉዳዮች በመቶኛ (%) |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ - 6 | ውልን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ280 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ300 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ300 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 7 | ከውል ውጪ ያለ ግንኙነትን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ240 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ350 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ350 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 8 | ይዞታ፤ ሁከት እና የቤት ኪራይ ውልን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ 105 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ120 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ120 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ - 9 | አጭር ስነ-ስርዓት የሚታዩ ጉዳዮች | በ60 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ75 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ90 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 10 | ባንክና ኢንሹራንስ ጉዳዮች | በ 90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ 150 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ180 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 11 | የንግድ ህጉን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች | በ150 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ240 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ300 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ300 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 12 | ውርስ ሃብት ለማጣራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ120 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ150 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ210 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ210 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 13 | ከውርስ ሃብት ክፍፍል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ150 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ180 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |
| መንገድ 14 | ከስራ ክርክር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች | በ40 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ50 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ60 ቀናት ውስጥ | | |
| | | *ከ60 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ 15 | የፍርድ አፈጻጸም ጉዳዮች | በ90 ቀናት ውስጥ | | |
| | | 180 ቀናት ውስጥ | | |
| | | በ365 ቀናት ውስጥ | | |
| | | ***ከ365 ቀናት በላይ የሆናቸው ጉዳዮች** | | |